# አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ

Editor's Note ቁጥር 2/2004

## ቢራቢሮ ቂጧን የምትሸፍነው የላት ምድር ታለብሳለች

### በቅርቡ ፋሺሽቱ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አሳተመ ስለተባለው መጽሐፍና ህትመቱን ለሽያጭ ስላበቁለት የታሪክ ማፈሪያዎች የተሰጠ ሀታታ

የመንግሥቱ ኃይለማርያም መንግሥት ባደረገው ጭፍጨፋ አንድ ትውልድ እንደመተረ የሚታወቅ ነው። ይህ የግፍ ዘመን በኢትዮጵያ ሕዝብ ኅሊና ውስጥ የማይጠፋ ቁስል አስቀምጦ አልፏል። ከደርግ ኢሠፓ መውደቅ በኋላ በቦታው የተተካው ወያኔም ይህንን የሕዝብ ቁስል እንዳይጠግግ በዘር ፖለቲካ እያባባሰው ሄዶአል። ይህን እኩይ ፀረ-ህዝብ ተግባራት ለመቀልበስ በተደረገው የሞት የሽረት ትግል፣ በርካታ ብርቅዬ፣ የኢትዮጵያ ልጆች የተሰውበት መሆኑ ይታወቃል።

በተለይ በደርግ ዘመነ-መንግስት ቀደምት ህዝባዊ የነፃነት ትግል ፋና ወጊ የሆነውን፣.... የዛን ትውልድ ታሪክ ለመበረዝና ደብዛውን ለማጥፋት በተደረገው ርብርብ፣ ደርግ፣ ወያኔና ሻዕብያ በፊት አውራሪነት ተሰለፈው ታሪክ የማይዘነጋው ጉዳት ያደረሱበት ቢሆንም፣ ይኸው አጋጣሚ በተጓዳኙ ሌሎች ድብቅ አጀንዳ ያላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች የባንዳነት ተልእኳቸውን እንዲወጡ አስችሏቸው እንደነበር ይታወቃል፡፡ እነዚህ ድርጅቶችና ግለሰቦች፣ በተለየዩ ጊዜያት በንፁሃን ወገኖች ላይ የተለያዩ ጥቃቶች በማድረስም ሆነ፣ እንዲደርስ በማድረግ ረገድ፣ የነበራቸው አብይ ሚና ከፍተኛ እንደነበር የሚታወቅ ነው።

ዛሬም ቢሆን በመተካካት ስሌት፣ አመች ጊዜ እየጠበቁ እንደ አሜባ እራሳቸውን የሚያባዙ፣ ለሕዝብ አርነትና ዲሞክራሲያዊ መብት መከበር ሲታገሉ የወደቁ ጓዶቻችን ላይ የሚያሾፉ፣ ለሌላ የሀገር ጥፋትና በደል ዋርድያ የቆሙ፣ የጎሳ ነውጥ ለማቀጣጠል የሚሸቀዳደሙ፣ የሀገርና የህዝብን ጥቅም አሳልፎ ለመስጠት በክህደት የሚደራደሩ፣ የአንድነት ሃይሎችን ትግል የሚኮንኑ፣ ሥራቸውን ለማጉደፍ ውስጥ ውስጡን ተግተው የሚሰሩ አልታጡም። ለዚህም መሰሪ ተግባራቸው ማረጋገጫ የሚሆነን ደግሞ፣ ባገኙት አጋጣሚ ብቅ እያሉ፣ ከዛ አስከፊና ትውልድ ጨራሽ የጭፍጨፋ ማእበል የተረፈውን ድርጅትና ደጋፊ አባላቱን ስም በማጉደፍ፣ አዲስ የተልዕኮ ግንባር ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ ፈጥረው መንቀሳቀስ መጀመራቸው ነው።

በአሁኑ ወቅት እንደሚታየው፣ ከደርግ ውድቀት በሁዋላ አድፍጦ፣ አመች ጊዜ ሲጠብቅ የቆየው፣ የመንግሥቱ ኃይለማርያም ፋሽስታዊ ቡድን፣ አንገቱን በማቅናት፣ ወቅታዊና አንገብጋቢ የሆነውን፣ ሀገርን ከወያኔ የጥፋት ተልእኮ የማዳን ህዝባዊና ሀገራዊ ተልእኮ ወደጎን በመተው፣ በንፁሃን ዜጎች ደም በጨቀዩ እጁ ያቦካውን ከፋሽሽት የጥፋት ገፈት የተቀዳ የታሪክ ቅርሻት መድብል፣ ምርጥ ታሪክ መፅሐፍ ነው ስሙት፣ በማለት ሊሞግቱን አደባባይ እየወጡ ያሉ ምንደኞች ተልእኮ፣ ምን ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መገመት አያዳግትም።

# አሲምባ ርዕስ አንቀጽ

Editor’s Note ቁጥር 2/2004

ይህ ሃላፊነት የጎደለው ተግባር፣ የኢትዮጵያን ወጣቶች ፅኑ የመብት ተጋድሎ ታሪክ፣ ህዝባዊነት በመካድ፣ ደርግ በሀገሪቱ ላይ ያደረሰውን መጠነ ሰፊ መረን የለቀቀ የጭካኔ ተግባር፣ ለማድበስበስና ከታሪክም ተወቃሽነት ለማስመለጥ፣ የሚደረግ መፍጨርጨር ከመሆኑ ባሻገር፣ መንግሥቱና ግብረ-አበሮቹ፣ በመቃብራቸው አፋፍ ላይ ቆመው በሚያሰሙት የንዛዜ ቃል ሽያጭ፣ ትርፍ ለማጋበስ የሚደረግ ሩጫ እንጅ ከቶ ሌላ ሊሆን አይችልም። ሌላው ይቅርና ዜጋውን ገሎ ሬሳ የሸጠ መንግስት መሪ ብእር ምን ሊተፋ እንደሚችል የሚጠፋው ያለ አይመስለንም። ዛሬ የጭፍጨፋው መሪ ተዋናይ መንግሥቱ ኃይለማርያምን ጨምሮ፣ ሌሎች የጥፋቱ መልእክተኞች፣ እያደረጉት ያለው የደርግን ወንጀለኝነት የማስተባበልና መንፈሱን እንደገና የማቅናት ሥራ ከነሱ አልፎ ድብቅ አላማ ባላቸው በሌሎች ተለጣፊዎችም ዘንድ ድጋፍ እየተቸረው ያለ ጉዳይ መሆኑን እያስተዋልን ነው።

ይህ ድርጊት ፈር እየለቀቀ፣ “ተራራውን ያንቀጠቀጠ ትውልድ“ በሚል፣ ወያኔ በቅጥረኛ ጸሐፍት፣ በአንድ በኩል ታሪኩን በመበረዝና በማባዛት፣ ለግል የድርጅት ዝናና ጥቅም ሲያውለው፣ በሌላ በኩል ደግሞ የደርግ ኢሠፓ መርማሪ፣ ቀንደኛ የቀይ ሽብር፣ ኮኮቦች ተዋናይ የነበሩ እነ ተስፋዬ ርስቴ ከወያኔ ጋር በመተባበር ”ምስክርነት ከባለሥልጣኑ አንደበት“ በሚል ሲነግዱበት ነበር።

እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ ፋሽስቶች የሚፅፉት እውነትን ሳይሆን ሲያራምዱት የነበረውን የፖለቲካ መስመር ሲከላከሉ ነው የሚታየው። ያፈሰሱት ደም ሳያንሳቸው፣ በቀጣይ ለሌላ ጥፋትና እልቂት ሊዳርጉን እንደሚሹ፣ መፃህፍታቸውን ያነበበ ሁሉ የሚረዳው ነው። መንግሥቱም በተለመደው ክህደቱ፣ በፃፈው መፅሃፍ በኢትዮጵያ ልጆች ደም ድጋሜ ለማፍሰስ እተፍጨረጨረ ባለበት በአሁኑ ወቅት፣ አንዳንዳንድ ፍርፋሪ ጠባቂዎች፣ መንግሥቱ ለትርፍ አይደለም የሰራው ብለው ሊያሳምኑን ይታገላሉ። ነገር ግን መንግሥቱ በገንዘብ ምክንያት ከሌሎች አሳታሚዎች ጋር ጭምር፣ በገንዘቡ ጉዳይ ሲደራደር እንደነበር የሚታወቅ ነው።

የሰሞኑም የፀረ-ኢሕአፓ ዘመቻና የክህደት ርብርብ ይኸው ነው። መንግሥቱ ኃይለማርያምና አመራሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጭዳ አርገው ስልጣናቸውንና ሓብታቸውን ያዳበሩት አልበቃ ብሎ፣ በታሪክ መጽሐፍ ስም ትርፍ ለመሰብሰብ የተጀመረው ጥረት አሳዛኝም አሳፋሪም ተግባር ነው። መጀመሩ ይህ ግለሰብ ምን ዓይነት ለጥቅሙ የቆመ ሰው እንደሆነ ያሳየናል። ያን ሁሉ ሕዝብ ከፈጀ በኋላ አሁንም ምንም ትምህርት እንዳላገኘ እንረዳለን። ይህ ፋሽስት ሃገሪቷን አስከፊ ሁኔታ አድርሶ ፣ አንድ ትውልድ መትሮ ፣ በድርቅና በጦርነት ሃገሪቷን አጥፍቶ፣ ለራሱ መሸሸጊያ በዝምባቤ አጎቱን አሥራት ወልዴን ከሞስኮ አምባሳደርነት ወደ ዚምባቤ ቀይሮ፣ ሕዝቡን ለዚህ አስከፊ የወያኔ ዘረኛ መንግሥት አስረክቦ፣ ጥሎ መሄዱ ምን ዓይነት አሳፋሪ ተግባር መሆኑን አልተረዳውም።

ይህ ፋሽስት በዚውያም ትርፍ በማጋበስ ተግባሩ አብረውት የሚሮጡ አላጣም ። በዚህም ይህንን አሳፋሪ ተግባር ለማስፈፀም አብረውት የተሰለፉት የሚያገኙት ገንዘብ የንፁሃን ደምና ሥጋ መሆኑን ሊረዱት ይገባል። ዛሬ ዶክተር ብሎ መንግሥቱ የሚኮራባቸው ልጆቹን ዓይነት በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ወጣቶች እንደቀጠፈ አንድም ያልተናገሩ ምሁሮች ነን ባዮች ለፋሽስቱ ጥብቅና ቆመው ማየታችን የሚገርም ነው።

# አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ

Editor's Note ቁጥር 2/2004

ይህ ለፍርድ መቅረብ የነበረበትን ግለሰብ እንደ ጀግና ለመሳል የሚደረገው ጥረት በግልገል ፋሽሽቶች ቀጣይነት ማግኘቱ የሚያሳዝን ነው። „መንግሥቱ ሃገሩን ይወዳል" የሚል ባዶ ፕሮፖጋንዳ ሲያስተላልፉ የከረሙ እንዳሉ ሁሉ እንደገና ወደ ሥልጣን ቢመጣ ኢትዮጵያን ያድናታል የሚሉ የኢሠፓ ካድሬዎችም አልጠፉም። በተለይም የወያኔ የሻዕቢያ ቅጥረኞች የዛን ትውልድ ታሪክ ለመበረዝ ጥረት ማድረግ እንደጀመሩ የሚታይ ነው። እውነቱ ግን ኢትዮጵያን ለማፍርስ የሚያደርጉትን ጥረት ኢሕአፓ በቆራጥነት ስለተዋጋቸው ነው።

" እንኳን ዋሽተን በእውነትም እየጮህን እውር ነው የምንወልድው አለች" ውሻ እንዲሉ፣ በተመሳሳይ በልብ ወለድ ታሪክ ሽያጭ "ለትርፍ ኢትዮጵያዊ ፣ ለዜግነት ሻዕብያዊ" የሆኑ ሁሉ ገበተውበታል። ትላንት የአማራውን ደም ለማፍሰስ ታጥቀው ሲጽፉ የነበሩ ፣ ዛሬ ደግሞ ተቃዋሚ በመሆን  የሻዕብያን ጥቅም ለማስጠበቅ ረገድ ረድፍ የያዙ፣ በግ መሳይ ተኩላዎች፣ የቀበሮ ባህታዊ ተልእኳቸውን ለመወጣት ሲጥሩ እንመለከታለን ። ያልተባለ ፣ ያልተነገረ ፣ ያልተተገበረውን፣ በመጻፍ የመንግሥቱንና ደጋፊዎጬ እጅ እንዲዘረጉላቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይራወጣሉ። ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ደባቸውን አስቀድሞ ስለሚያውቀው ቁብ አይላቸውም። ከዚህ በፊት እንደታየው ሁሉ ወደፊትም በተመሳሳይ ይጋለጣሉ።

በአጠቃላዩ ሲታይ፣ ያልተገራ ፈረስና በአምባ ገነንነት የሚገኝ ሥልጣን አንድ ናቸው። ሁለቱም ልካቸውን አያውቁም፣ ሁለቱም መሄድ መቻላቸውን እንጅ መውደቂያቸውን የሚቃኙበት አይምሮ የላቸውም። ሁለቱም መተንፍስ እንጅ ማዳመጥ አይችሉም። ሁለቱም ሌጣ ልብ እንጅ ሚዘናዊ ህሊና የላቸውም። " በጅብ ጅማት የተሰራ ክራር፣ ሲመቱት እንብላው አንደሚል ሁሉ" እነሱም በባህሪያቸው እንዲያ ናቸው።

ከአሁን ወዲያ ከፋሽስቶችና ከዘረኞች ጋር በመቆም ቀጣይ እልቂት ለማካሄድ የሚማስኑት ሁሉ ከወዲሁ  እንደማይሳካላቸው ሊረዱት ይገባል። መንግሥቱም አይመለስም፤ ኢሠፓም በምንም አይነት ወደ ሥልጣን አይመጣም ። ይህ እንዳይሆን ደግሞ እውነተኛ የኢትዮጵያ  ልጆች የሚጠይቀውን ሁሉ መስዋእትነት ለመክፈል ወደ ኋለ እንደማይሉ ከወዲሁ ሊረዱት ይገባል ።

**ዶሮ ጮኸ ብለሽ፣ አትክፈችው ደጁን፣**
**ዶሮ ጠላቴ ነው፣ በልቼበት ልጁን።**

**መባሉን ልብ ይሏል!**

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !**